**Hawarya; vol.14; No3**

**June/July 2009 Edition**

# ህልም ህይወት፤

በሙቀቱ ቤቴ - መደብ ላይ ወለሉ፥
ቁንጫው ይምለጠኝ - አይማረኝ ትሁዋኑ፥
ሜዳ ላይ ከሚያሸኝ - ተባይ ምናምኑ፥
ከሚጫወትብኝ ጊንጥና ጉንዳኑ።

ትልቁ ቤታችን የተሠራው ድሮ
ጣራና ግድግዳው የቆመው ተዋቅሮ፥
ወለል መደብ አለው - በደም'ብ ተዘጋጅቶ፥
ስንቱ የተኛበት - ክንዱን ተንተርሶ፥
ቢርበው ቢጠማው - ህልሙን ህይወት አርጎ።

---------//-------

(ሙሉቀን)